**የኢቦላ ወረርሽኝን አስመልክቶ እየተከናወነ ያለውን የቅድመ ዝግጅት ተግባራትና ለኮሌራ ወረርሽኝ እየተሰጠ ያለውን የጤና ምላሽ <u>አስመልክቶ የተዘጋጀ ሳምንታዊ መግለጫ ሐምሌ 23/2011</u>**

## የኢቦላ ወረርሽኝን በተመለከተ

- የኢቦላ ወረርሽኝ ኢቦላ በሚባል ቫይረስ አማካኝነት የሚመጣ ገዳይ በሽታ ነው :: የበሽታው ምልክቶች ድንገት የሚጀምር ከፍተኛ ትኩሳት፣ የራስ ምታት ፣የሰውነት መዛል፣ ተቅማጥና ትውከት፣ በሰውነት ላይ የሚወጣ ሽፍታ፣ እንዲሁም በተለያዩ የሰውነት ቀዳዳዎች ወደ ውጭና ወደ ውስጥ የደም መፍሰስ ያስከትላል።
- የመተላለፊያ መንገዶችም ፦ ከበሽታው በተያዙ ሰዎች ደምና ከሰውነት በሚወጡ ፈሳሾች( ሰገራ፣ ሽንት፣አክታና የወንድ ዘር ፈሳሽ) አማካኝነት እንዲሁም በሽተኞቹ የተጠቀሙበትን ቁሳቁሶች(አልጋ፣ልብስ፣አንሶላ፣ጓንት፣ በህክምና ወቅት የሚለበሱ ልብሶችና ጥቅም ላይ የዋሉ የህክምና ቁሳቁሶች) ጋር በሚፈጠር ንክኪ፣
- ለበሽታው የተጋለጡ ሰዎች ምልክት የሚያሳዩበት ጊዜ ከ2-21 ቀናት ባሉት ጊዚያ ውስጥ ሲሆን ምክት ያልታየባቸው ሰዎች በሽታውን አያስተላልፉም።አንድ ሰው በበሽታው መያዙን ማረጋገጥ የሚቻለው በላብራቶሪ ምርመራ ብቻ ነው።
- ወረርሽኙ ቢከሰት ከፍተኛ ተጋላጭነት ያላቸው፡ የጤና ባለሙያዎች፣ የቤተሰብ አባላት፣ አስታማሚዎች እንዲሁም በግነዛ ወቅት አስክሬኑ ጋር ንክኪ የሚኖራቸው ሰዎች ናቸው።
- ከበሽታው የመከላከያ መንገዶች
    - እጅን መታጠብ
    - በበሽታው የተጠረጠሩ ሰዎች ከሚወጡ ፈሳሾች ጋር ንክኪ አለማድረግ
    - በኢቦላ በሽታ የሞቱ ሰዎች አስክሬን ከመንካት መቆጠብ

- በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎና ከ 2014 ጀምሮ የተከሰተ ሲሆን በአሁን ወቅት በሰሜን ኪቩ ፕሮቪንስ ወረርሽኙ ተቀስቅሶ የብዙ ሰዎችን ህይወት እየቀጠፈ ይገኛል። 2018 ጀምሮ በወረርሽኙም 2659 ሰዎች በበሽታው ተይዘዋል ከዚህም ውስጥ 1782 ሰዎች ህይወታቸው አልፏል።
- ሐምሌ 10፣ 2011 ዓ.ም የአለም ጤና ድርጅት በዲሞራቲክ ሪፐብሊክ ኦፍ ኮንጎ የተከሰተዉ ወረርሽን የአለም የህብረተሰብ ጤና ስጋት ነው ብሎ ማወጁ ይታወቃል።
- ከዚህም ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የኢቦላ ወረርሽኝ ወደ ሀገራችን እንዳይገባ እንዲሁም በበሽታው የተያዘ ሰው ቢኖር ለማከም  እንዲቻል የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ሲያከናውን የቆየ ሲሆን የአለም ጤና ድርጅትን አዋጅ መሰረት በማድረግ የቅድመ መከላከል ተግባራትን አጠናክሮ ቀጥሏል።
- እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ በሳምንት ውስጥ 25 ያህል በረራዎች ያደርጋል። ስለሆነም የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስትቲዩት  በአለም አቀፉ የጤና ደንብ (IHR 2005) መሰረት ከኮንጎ የሚመጡ ተጓዦች የሰውነት ሙቀትን በመለካት የልየታ ስራ እያከናወነ ይገኛል።
  - በቦሌ አለም አቀፍ አየር መንገድ፣ በድሬደዋ ፣ በመቐለ  እና ባህርዳር አለም አቀፍ አየር መንገዶች የሰውነት ሙቀት በመለካት የልየታ ስራ እየተሰራ ይገኛል። በተለይም ከዲሚክራቲክ ኮንጎ የመጡ መንገደኞች ከበሽታው ነጻ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በሀገራችን በሚቆዩባቸው ጊዚያቶች እስከ 21 ቀናት ድረስ ባሉበት ቦታ ክትትል እየተደረገ ይገኛል።በዚህ መሰረት፡-
    - የልየታ ስራ ከተሰራባቸው መንገደኞች ውስጥ 17,302 እስከ 21 ተከታታይ ቀናት ክትትል ተደርጎላቸዋል።
    - በአውሮፕላን ማረፊያ ጣቢየውም በበሽታው የተያዙ መንገደኞች ቢያጋጥሙ ለማከም የሚያስችል 2 የለይቶ ማቆያ ማእከል የተዘጋጀ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ በቦሌ ጨፌ የኢቦላ ለይቶ ማከሚያ ማዕከል ተዘጋጅቷል።
  - ከአየር ትራንስፖርት ከሚገቡ መንገደኞች በተጨማሪ በ18 የየብስ መግቢያና መውጫ ኬላዎች ላይ የሰውነት ሙቀት በመለካት የልየታ ስራ እየተሰራ ይገኛል።

- በጋምቤላ ክልል በልየታው ስራ ጊዜ በኢቦላ በሽታ የተጠረጠሩ መንገደኞች ሲገኙ ወደ ህክምና ጣቢያ እስኪወሰዱ ድረስ 5 የለይቶ ማቆያ ጣቢያዎች የተዘጋጁ ሲሆን የተሻለ ህክምና በመስጠት ለይቶ ለማከም የሚያስችል የህክምና ማእከል በጋምቤላ ከተማ ሆስፒታል ውስጥ ተዘጋጅቷል፡፡
- በተጨማሪም ኢንስቲትዩቱ ከ 290 በላይ የሚሆኑ የህክምና፣ የህብረተሰብ ጤናና ሌሎች ባለሙያዎችን በማሰማራት የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡የዚሁ አካል የሆነው የታማሚዎች ህክምና እና አያያዝ ላይ ዕለታዊ የተግባር ልምምድ በማድረግ ባለሙያዎቹ እራሳቸውን ብቁ እንዲያደርጉ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

**የኮሌራ ወረርሽኝን በተመለከተ**

- በኦሮሚያ ክልል በኮሌራ በሽታ የተያዙ ሰዎች ቁጥር 464 የደረሰ ሲሆን በባለፉት 2 ሳምንታት በሽታው በቦረና ዞን በሞያሌ ወረዳ 15 ሰዎች ላይና በምስራቅ ሀረርጌ ዞን በጎሮ ጉቱ ወረዳ 14 ሰዎች ላይ የተከሰተ ሲሆን አስፈላጊው ህክምና ተደርጎላቸዋል፤ እየተደረገላቸውም ይገኛል፡፡
- በሌሎች ክልሎችና በአብዛኛው ወረርሽኙ በተከሰተባቸው የኦሮሚያ ክልል ወረዳዎች ወረርሽኙ በቁጥጥር ስር ውሏል፡፡
- በተለያዩ ጊዜያት በተከናወኑ የቅድመ መከላከል እንቅስቃሴዎች፤የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራት (በተለያዩ ሚዲያዎች፣ ት/ቤቶች፣ ብዙ ህዝብ በሚሰበሰብባቸው በአላት ላይ በማስተማር)፣ ህብረተሰቡ በወሰዳቸው የጥንቃቄ ተግባርት እንዲሁም በተሰጡ የጤና ድጋፎች ክትባትን ጨምሮ ወረርሽኙ ሊቀንስ ችሏል፡፡ ይሁንና ማህበረሰቡ በዚህ ሳይዘናጋ አሁንም አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ እናሳስባለን፡፡

**የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት**

**ሐምሌ 23 / 2011 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**